# የወንጌል ኃይል

## በእምነት የሚገኝ ፅድቅ (ክፍል 3)

*"አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።"*

*(ሮሜ 4፡3)*

አብርሃም የፀደቀው በስራው አይደለም “አብርሃም በስራ ፀድቆ ቢሆን ኖሮ፣ የሚመካበት ነብረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት መመካት አይችልም። መፅሐፍስ ምን ይላል? ‘አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት” (ሮሜ 4፡2-3)። አብርሃም ልጅ ተወልዳለህ ብሎ እግዚአብሔር የገባለትን ቃል በማመኑ ፅድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንጂ በመገረዙ ወይም በሌላ ሰራው አይደለም ጽድቅን ያገኘው። ዳዊትም በሌላ መልኩ በስራው ኃጢአተኛ እንደሆነ ነገር ግን በእምነት ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ጽድቅ ሲያመለክት “መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣ ኃጢአታቸው የተሰረየላቸው፣ ብፁአን ናቸው። ኃጢአቱን ጌታ ከቶ የማይቆጥርበት ሰው ብፁእ ነው” (ሮሜ 4፡7-8) ይላል።

እንዲሁም የአብርሃም ፅድቅ ህግን በመፈፀም እንዳልመጠ ጳውሎስ አስረግጦ ይናገራል “እርሱ የዓለም ወራሽ እንዲሆን አብርሃምና ዘሩ ተስፋን የተቀበሉት በሕግ በኩል አልነበረም፤ ነገር ግን በእምነት ከሆነው ፅድቅ ነው” (ሮሜ 4፡13)። ይኸውም አብርሃም ህግ ከመምጣቱ ከብዙ ምእተ አመት በፊት የኖረና በዚያ ጊዜ ‘የዓለም ወራሽ ትሆናለህ’ ተብሎ መነገሩ ምስክር እንደሆነ በመጥቀስ ነው (ገላ. 3፡17)። እንደውም ሕግን በመጠበቅ ፅድቅን ለማግኘት የሚሞከር ሙከራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደሚያመጣ ይገልፃል።
የአብርሃም ፅድቅ ግን የመጣው በእምነት ነው። እርሱም ሆነ ሚስቱ ሳራ ልጅ መውለድ በማይችሉበት ጊዜ “ለሙታን ህይወትን በሚሰጥ፣ ያልነበረውንም እንደነበረ አንደ ነበረ በሚያደርግ” (ሮሜ 4፡17) በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን በማድረጉ ፅድቅ ሆኖ ተቆጠረለት “የብዙ ህዝብ አባት” ተብሎ ተጠራ።

እኛም አስቀድመን የደህንነታችን ሚስጥር የሆነውን፣ የሌለውን ወደ መኖር በሚያመጣ፣ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ድንቅ አሰራር ምንም ዋጋ ሳንከፍል በእምነት የሆነ ፅድቅ እንደተደረገልን ልንገነዘብ ያስፈልገናል፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ያዘጋጀውን፣ በእምነት የሚገኘውን የምስራች ቃል በየደረስንበት እንድናበስር ጌታ ሁላችንንም ይርዳን።